# 5. ተረካዊ ስነ-ምግባር በአማርኛ ስነ-ጽሁፍ ውስጥ፤ ታሪካዊ ዳሰሳ

**በደመቀ ጣሰዉ (ዶ/ር)፣ የኢትዮፕያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ፤ email: demeketasew123@gmail.com**

***አጠቃሎ***

*ስነ-ጽሁፍ ስነ ምግባርን ለማስተማር አይነተኛ ማሳሪያ እነደሆነ የማይታበል ሃቅ ነዉ፤ ሆኖም ስነ-ጽሁፍ የሚጻፍበት እና የሚነበብበት የራሱ የሆነ ስነ ምግባርም አለዉ፡፡ ይህንንም ምሁራን ተረካዊ ስነ-ምግባር (narrative Ethics) በማለት ይጠሩታል፡፡ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የዘመናዊ አማርኛ ስነ-ጽሁፍ ከዉልደቱ ጀምሮ አሁን እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ ከተረካዊ ስነ-ምግባር አንጻር የተስተዋሉ ለዉጦችን ለመዳሰስ ያለመ ነበር፡፡ ጥናቱ ዘመናዊ አማርኛ ስነ-ጽሁፍን ታሪክ በአብዛኛዉ ምሁራን በሚስማሙበት በአራት የታሪክ ምዕራፍ (ማለትም፡ ቅድመ-ጦርነት (ከ1928-32)፣ ድህረ-ጦርነት (ከ1932-1966)፣ ድህረ-አብዮት (1966-1983) እና የአሁኑ ዘመን (ከ1983 ወዲህ)) በሚል በማካፋፈል በየታሪክ ምእራፉ ምን አይነት ተረካዊ ስነ-ምግባር እንደሚስተዋል ተንትኗል፤ በየታሪክ ምእራፉ የተስተዋሉ ልዩነቶችን ለይቷል፤ እንዲሁም ተረካዊ ስነ ምግባር በየታሪካዊ ምእራፉ ያለዉን አንድነት እና ልዩነት አወዳድሯል፡፡ እነ ዚህን ጥናታዊ አላማዎች ለማሳካት ስነ ተረክ (narratology) እንደ መተንተኛ ጽንሰ-ሃሳብ ያገለገለ ሲሆን ተረካዊ ትንታኔ (Narrative analysis) ደግሞ ከቀዳሚ እና ሁለተኛ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን ጥቅም ላይ የዋለ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ነዉ፡፡ የመረጃዎችን ትንታኔ ማሳረት በማድረግ የተደረሰበት የጥናቱ ግኝት ተረካዊ ስነ-ምግባር በአማርኛ ስነ-ጽሁፍ ዉስጥ በሁሉም ታሪካዊ ምእራፎች በተመሳሳይ ሚዛኑ እንደማይስተዋል፤ ይልቁንም የአማርኛ ስነ-ጽሁፍ ተረካዊ ስነ-ምግባር ከምዕራፍ ምዕራፍ እየተዳከመ እና ስነ-ጽሁፉም ይበልጥ ኢ-ስነ-ምግባራዊ እየሆነ እንደማጣ ያሳያል፡፡*

***ቁልፍ ቃላት፡*** *- ተረክ፣ ተረካዊስነ-ምግባር፣ ስነ-ተረክ፣ ተረካዊትንታኔ*

## *1. መግቢያ*

አማርኛ ቋንቋ ግዕዝን ተክቶ የቤተመንግሰት ቋንቋ ከሆነበት ግዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያበረክት ቆይቷል በማበርከት ላይም ይገኛል፡፡ ሆኖም ምሁራን በአብዛኛዉ እንደሚስማሙበት አማርኛ የስነ ጽሁፍ ቋንቋ የሆነዉ ከ19ኛዉ ክ/ዘመን ጀምሮ ነዉ፡፡ (ታደሰ እና አሊ 1995፡ 17) ከዚህ ግዜ ጀምሮ ኢትዮጵያዊያን በርካታ ጠቃሚ ሃይማኖታዊ እና አለማዊ የስነ ጽሁፍ ስራዎችን በዚሁ ቋንቋ ሲያበረክቱ ቆይተዋል፤ በማበርከት ላይምይገኛሉ፡፡

ዘመናዊ ልብወለድ በአማርኛ መጻፍ ከተጀመረ ከአንድ ክፍለ ዘመን በላይ ሆኖታል፡፡ በ1900ዓ/ም የታተመችዉ እና ለንባብ የበቃችዉ የአፈወርቅ ገብረ እየሱስ "ልብወለድ ታሪክ"

ዘመናዊ ስነጽሁፍን ለአማርኛ ያስተዋወቀች የመጀመሪያዋ ልብወለድ ናት፡፡ አሁን የምናነባቸዉ፣ የምናጠናቸዉ እና የምንተነትናቸዉ በርካታ የአማርኛ ስነጽሁፍ ስራዎች የተገኙት የዚችን ልብወለድ ዉልደት ተከትሎነ ዉማለት ይቻላል፡፡

የአማርኛ ስነ-ጽሁፍ እድገት እና ታሪክ በተለይምከይዘት እንጻር በብዙ የአገር ዉስጥምሆነ የዉጭምሁራን ተጠንቷል፣ ተተንትኗል (ምንምእንኳ በቂ ነ ዉለማለት ባይቻልም)፤ ሆኖምየዚህ ስነ-ጽሁፍ ቅርጻዊ ማንነቱ በቅጡአልተዳሰሰም፤ ዘማናዊዉን የስነጽሁፍ ጥናት ጽንሰ-ሀሳብ እና አንድምታ ማዕረት አድርጎ የተሰሩ ጥናቶች እጅግ ዉስን ናቸዉ፡ በመሆኑምየዚህን ስነ-ጽሁፍ ስነ ዉበትምሆነ ጭብጥአጉልተዉየሚያሳዩ ጥናቶች አስፈላጊ ናቸዉ፡

ይህ ጥናት በዚህ ረገድ ያለዉን የእዉቀት ክፍተት ለመሙላት የሚያግዝ አስተዋጽኦ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነዉ፡ ጥናቱ በአማዛኙ ቅርጽ ላይ የሚያተኩር ሲሆን የስነ-ተረክ (narratology) ጽንሰ-ሃሳብን ማዕረት አድርጎ በተለይም የአዉዳዊ ስነ-ተረክ (contextual narratology) አስተሳሰቦች ላይ ተመርኩዞ ለማጥናት ይሞክራል፡፡

ስነ-ተረክ፣ ተረክን (narrative) የሚያጠና የስነ-ጽሁፍ ጽንሰ-ሃሳብ ሲሆን ዘማናዊ ከሆኑት መካከል በከፍተኛ ደረጃ አለማቀፋዊ ተቀባይነት እያገኘ ያለ እና ከስነጽሁፋዊ ጥናቶች ባሻገርምለሌሎች የጥናት ማከኮች እንደ ጥናት ስልት ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኝ ነዉ፡ ስነ-ተረክ አንድን የስነጽሁፍ ስራ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለመተንተን የሚያስችሉ በርካታ የማጥኛ ስልቶችን እና አስተሳሰቦችን የያዘ ሰፊ ጽንሰ-ሃሳብ የያዘ ሲሆን ከነዚህ ዉስጥም አንዱ እና በኢትዮጵያ የስነጽሁፍ ጥናት ዉስጥ እስካሁን በቅጡአግለግሎት ላይ ያልዋለዉ ተረካዊ ስነ-ምግባር (narrative ethics) ይገኝበታል፡፡

በዚህ ጥናት ተረካዊ ስነምግባር በአማርኛ ስነጽሁፍ (በተለይምበአማርኛ ልብወለድ ስራዎች ላይበማተኮር) ዉስጥእንዴት እንደ ሚታይ ለመዳስ ይሞክራል፡፡ የስነ-ጽሁፉን ታሪካዊ እድገት ተከትሎምተረካዊ ስነ-ምግባር እየተሸሻለ ነ ዉወይስ እየደከመነ ዉየሚለዉን ጥያቄ ለመሙላስ ይሞክራል፡፡

**2. የቁልፍ ቃላት ትንተና**

ከርእሱ ለሚረዳት እንደሚቻለዉየዚህ ጥናት ትኩረት ተረካዊ ስነምግባር በአማርኛ ስነ-ጽሁፍ ዉስጥ ምን ይመስላል የሚል አብይ ጥያቄ መሙላስ ላይ ነዉ፡ ሆኖምይህን ጥያቄ ከመሙላሳችን በፊት ተረካዊ ስነ-ምግባር ምንድን ነዉየሚለዉን ጥያቄ ማብራራት የግድ ላል፡፡ የተረካዊ

ስነ ምግባርን ምንነት ለማብራራትም በቅድሚያ ተረክ ምንድን ነዉ የሚለዉን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ተረክ ምንድን ነዉ የሚለዉን ጥያቄ በመመለስ ሂደት በርካታ ምሁራን ለበርካታ ጊዜያት ሲከራከሩበት እና ሲወያዩበት ቆይተዋል ክርክሩ አሁንም እንደቀጠለ ነዉ፤ በመሆኑም አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ ለማስጠት ያስቸግራል፡፡ ሩድረም(2005፡ 1-2) የራሱን ሳይጨምር ከዘጠኝ በላይ በተለያዩ ምሁራን ስለ ተረክ የሰጧቸዉን ብያኔዎችን ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይህም የተረክ ብያኔ ምን ያክል ስምምነት ላይ ያልተደረሰበት መሆኑን ያሳያል፡፡ ሆኖም በሁሉም ብያኔዎች ዉስጥ ተደጋግሞ የተገለጸ እና እንደ ተረክ ማለያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ሃሳብ አለ፡፡ ምንም እንኳ የሁነቶች ብዛት ና የአደራደር ሁኔታ ከምሁር ምሁር የተለያየ ቢሆንም ሁሉም ብኔዎች አንድን ተረክ ተረክ ነዉ ለማለት በዉስጡ ቢያንስ አንድ ሁነት በሆነ ዓይነት ቅደምተከተል ተሰንዶ ማግኘት እና በሆነ አካል መተረክ አለበት ይላሉ፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳዉ ጥያቄ በተረክ ዉስጥ የሚገኘዉ ሁነት ወይም ድርጊት ምን አይነት ነዉ? እንዴትስ ይደረደራል? ማንስ ነዉ ስለ ድርጊቶቹ እና አደራደራቸዉ የሚነግረን? የሚሉት ናቸዉ፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች በተገቢዉ ሁኔታ በመመለስ ተረክን በዳበረ መልኩ ማብራራት የቻለዉ የስነ ተረክ አባት ተደርጎ የሚቆጠረዉ ጌራርድ ጀነት (1980፤ 1988) የተባለ ምሁር ሲሆን ተረክን የሶስት ክፍሎች የእርስበርስ ግንኙነት ዉጤት አድርጎ ያቀረበዉ ምሁራዊ ትንታኔ እስካሁን ሰፊ ተቀባይነት ያገኘ ሃሳብ ነዉ፡፡ እንደ ጀነት (1980) ገለጻ ተረክ ሶስት ክፍሎች አሉት እነሱም፤ ዲስኩር (discourse) ወይም "ተረክ" ይለዋል፣ ታሪክ (story)፣ እና ትረካ( narration) ይባላሉ፡፡ ከነዚህ ክፍሎች ዉስጥ ለጀነት ጠቃሚዉ እና በስነ-ተረክ ጽንሰሃሳብ ሊጠና የሚገባዉ ቀዳሚ ክፍል ትረካ ነዉ፡፡ እንደሱ አገላለጽ ትረካ ለታሪክም ሆነ ለ ዲስኩር ማሳረት ነዉ፡፡ አንድ ሰዉ መተረክ ሲችል ታሪኩን ይናገራል፤ ታሪኩን በትረካ መልክ ሲያቀርብ ደግሞ ዲስኩር ይፈጠራል ይላል፡፡ በዚህ እሳቤ ማሳረት ጀነት በተረክ እና በትረካ ወይም "በተነገረዉ" እና "በአነጋገር" መካከል ልዩነት መኖሩን አሳይቷል፡፡ የስነ-ተረክ ማሳረትም ይህ ልዩነት ነዉ፡፡ ይህን እሳቤ ማሳረት በማድረግም በአተራረክ፣ በታሪክ እና በ ተረክ በእያንዳንዳቸዉ ስር ምንምን ስነ-ጽሁፋዊ አላባዉያን እንደሚከተቱ ተንትኖ አቅርቧል፡፡ በእሱ ትንታኔ ማሳረትም ተረካዊ ስነ-ምግባር በ አተራረክ ዉስጥ የሚገኝ አንድ አላባ ነዉ፡፡

እንደ ጀምስ ፊላን (2013፡ 23-24) ገለጻ ተረካዊ ስነ ምግባር በታሪክ እና በትረካ እንዲሁም በ ስነ-ምግባራዊ እሴቶች (moral values) መካከል ያለዉን ተዛምዶ ይመለከታል፡፡ ተረካዊ ስነ-ምግባር ስነ ምግባራዊ እሴትን የታሪክ እና የትረካ ማስተሳሰሪ ገመድ አድርጎ ይወስዳል

ምክንያቱም ተረክ በራሱ በግልጽም ሆነ በሽፍን አንድ ጸሃፊ ፣ ተራኪ ፣ ገጸ-ባህሪ፣ ወይም ተደራሲ በተረክ ዉስጥ እንዴት ያስባል፣ ይገመግሟል እና ተግባሩን ይፈጽሟል የሚለዉን ጥያቄ እንድንጠይቅ ስለሚያስገድደን፡፡ ሥለሆነ ምተረካዊ ስነ-ምግባር ማለት በተረክ እና በትረካ መካከል ምን አይነት ስነምግባራዊ እሴት አለ ሚለዉን ሚዳስስ የጥናት ማክ ነዉ ማለት ይቻላል፡፡

የተረካዊ ስነ-ምግባር ጥናት ሰፊ እና በርካታ ጥቄዎችን እያነሳን ሚልስ ማስጡት የምንችልበት መሆኑን ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ፊላን (ዘኒከሜሁ) እነዚህን ጥያቄዎች በአራት ከፍሎ አቅርቧቸዋል፤ "1) the ethics of the told, 2) the ethics of the telling, 3) the ethics of writing/producing and 4) the ethics of reading/reception. " ፊላን ከጠቀሳቸዉአራት ጥያቄዎች መመካከል ቀደምሲል ስለ ተረክ ባስቀመጥነ ዉ ብያኔ ማስረት የዚህ ጥናት ትኩረት በመጀመሪያዉ እና በሁለተኛዉጥያቄ ላይ ብቻየተማሰረተ ይሆናል፡፡

በዚህም ማስረት የመጀመሪያዉትያቄ ትኪረት ሚያደርገዉበገጸ-ባህሪያት እና ድርጊቶች ላይ ሆኖ ፤ የገጸባህርያት ድጊቶች (በተለይምየማ ቡበት ግጭቅ እና ግጭቱን ለመፍታት የሚወስዱት አማራጭ) ስነምግባራዊ ምህዳር ፣ የገጸ-ባህሪያት የእርስበርስ ግንኙነ ት ስነምግባራዊ ሁኔታ ምን ይማስላል የሚሉትን አይነት ጥያቄዎች ለመመለስ ይጥራል፡፡ ሖለተኛዉ ጥያቄ ደግሞ የልብወለዱ ዉስጣዊ ጉዳዮች በተለይም በተራኪዉ እና በትረካዉ ላይ አተኩሮ የእነዚህን ስነምግባራዊነ ትየሚጠይቅ ነዉ፡ በዚህምተራኪዉለትረካ የተጠቀማበትን ቋንቋ ፣ የድርጊት አደራደር እና የታሪክ ሚ ጣ ስነ-ምግባራዊነ ት በተደራሲዉ ላይ የሚፈጥረዉን ስነምግባራዊ ዉጤት ለመተንተን ይሞክራል፡፡

የአንድን የስነ ጽሁፍ ስራ ተረካዊ ስነምግባር ለማጥናት በሚሞከርበት ጊዜ ትኩረት ሊሰጣቸዉ የማ ቡ ጉዳዮች አሉ፡፡ ከነዚህም ዉስጥ አንዱ ፈሬይ (1995፡ 58) እንደሚጠቁመዉ ስነምግር የሃላፊነ ት ጉዳይ ነዉ፡ የደራሲዉ፡ የተራኪዉ፣ የገጸ-ባህሪያት ሃላፊነ ት፡፡ ስለሆነ ም ስነምግባራዊ ጥናትእነዚህ አካላት የሚጠበቅባቸዉን ስነ-ምግባራዊ ሃለፊነ ት ተወጥተዋል ወይ; የሚለዉን ጥያቄ ለመመለስ መሞከር ይኖርበታል፡፡

የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረትም በአማርኛ ስነጽሁፍ ዉስጥ እነዚህ አካላት ስነምግባራዊ ሃላፊነታቸዉን በመወጣት ረገድ ያለዉ ሁኔታ ምን እንደሚማስል ከታሪካዊ አዉድ አንጻር ማጥናት ነዉ፡ ሆኖምየእነዚህን አካላት ሰነምግባራዊ ግዴታ ለማጥናት ሲሞከር በሄትኛዉ የዘመን እና የማህበረሰብ ሰነምግባራዊ አዉዶች ዉስጥ ማጥነ ት ይቻላል ስነምግባር በዘመን

የሚወጥ እንደማህበረሰቡም ስሪት ሚያይ አይደለም ወይ ሜል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ በርግጥ እንዲህ ያሉቱ ትያቄዎች አግባብነት ያላቸዉ ናቸዉ፡ ሆኖም ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ ተረካዊ ስነ-ምግባር ከሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች ዉስጥ ሁለቱ እና በዋነኝነት መጽሀፍን ማስረት አድርገን ልንሜለሳቸዉ በምንችላቸዉ ጥያቄዎች ላይ ብቻ እንድናተኩር የተደረገበት ምክንያት ይኸዉ ነዉ፡ በሚሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት ትረካ ላይ ስለሆነ የአማርኛ ስነ-ጽሁፍን ተረካዊ ስነ-ምግባር በመተንተን ረገድ በየዘመኑ ያለዉን ማህበረሰባዊ አስነ ምግባር እንዴት በልብወለዶቹ ዉስት ተንጸባረቀ የሜል አቀራረብ ሳይሆን ያለዉ የኢትጵያ ስነ-ጽሁፍ ሊኖረዉ ሚገባዉን የስነ ምግባር ደረጃ ይዟል ወይ የሚለዉን ጥያቄ ለመሟለስ የሚቱር ነዉ፡ ዕዚህ ላ ሌላ ማስረታዊ ትያቄ ማ ሳቱ ግድ ኑዉ፡ ለሚሆኑ የኤትዮጵያን ስነጽሁፍ በጠቅላላዉ የአማርኛ ስነጽሁፍን በተናጥል ሊገልጽ የሚችል የስነ ምግባር ደረጃ አለን; ይህ ጥያቄ ማስረታዊ ከሚሆኑም ባሻግር ወደፊት ጠንከር ያለ ምርምር የሚፈልግ እንደሆነ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ያምናል ሆኖምለዚህ ጥናት እንደ መ ሻ ሊያገለግለን የሚችል ሃሳብ በፍልስፍና ምሁሩ ክላዉድ ሳምን ር (1985፡ 427) ቀርቦልናል፡፡ ሳምን ር የኢትጵያዊያንን የአአጻጻፍ ሰስነ-ምግባር ከአዉሮጳዉያን ጋር እያነጻጸረ እንዲህ ይተነትነዋል (ለሃሳብ ማትነት ሲባል ጥቅሱ የተወሰደዉ በተገኘበት ቋንቋ ነዉ፡

> Whereas, the Western world has a tendency to consider things as they are in their impersonal objectivity, the Ethiopian […] world is clearly anthropocentric. The westerner takes as its starting point the world of external reality, which is distinct and measurable. The […] Ethiopian does not break away from the world in which he leaves. He does not disengage himself from it, he does not stand out; he is part of it. His starting point is within himself, in his own personal experience. He does not try to express what is in his mind: he rather attempts to evoke it […] The Westerner reconstructs and recreates the outside world with the framework of his own thought. The Ethiopian starts from what is already in his mind and endeavors to transmit it by suggestion […] the westerner would liketo conceive truth and to demonstrate it; the […] Ethiopian seeks tooffer himself to it and to have it desired by others. The western world is the world

በርግጥ ሳምን ር ይህን ሃሳብ የሰነዘረዉ ስለኢትጵያዊያን ቀደምት የግዕዝ ስነጽሁፍ ሊቆች ነዉ፡ ሆኖም የአማርኛ ስነጽሁፍ መ ሻ ይኸዉ የግእዝ ስነጽሁፍ በሚሆኑ የአጻጻፍ ልማዱም

የቀደመዉን ማማሳል እንደሚኖርበት አያከራክርም፡፡ በተለይም ሳምን ር የጠቀሳቸዉ ተረካዊ ስነምግበርን የሚሞላከቱ በሚሆናቸዉ አማርኛ ስነ-ጽ ሁፍን ከነዚህ የስነምግባር ማሳረቶች አንጻር ማ ምግ ምተገቢነዉ፡፡

ከጥቅሱ ለሚረዳት እንደሚቻለዉ ኢትዮጵያዊያን ጸሃፍት ሶስት ማሳረታዊ ስነምግባራዊ ልማዶች አሏቸዉ፡ እነሱም 1) ሰዋዊ ጉዳች ላይ ማተኮር ወይም ለሰዉ የሚሰጠዉን ክብር አለማጓደል ፣ 2)የሚኖርበትን ማህበረሰብ አለሚርሳት፤ የማህበረሰቡን ባህላዊ፣ ማህበረሰባዊ እሴቶች ማክበር ፣ 3) በጽሁፉ የማ ልጸዉ ሃሳብ የራሱ ብቻ ሳሆን ማህበረሰቡም ሚሆኑን ሚረጋገጥ እና 4) ማህበረሰባዊ ሂሶችን ሲሰነዝር በነቀፌታ ሳሆን በምክር ሜልክ ሚድረግ ናቸዉ፡፡ እነዚህ ሶስት ባህርያት እንደ ስነ-ምግባር ማሳረቶች ተደረገዉ ሊወሰዱ ይችላሉ ምክንያቱም በአንድ የልብወለድ ስራ ዉስጥ የሚስተዋሉ የትረካ እና የተረክ ስነምግባሮች ከነዚህ የጸሃፍት ሃለፊነት ዉጭአይደሉምእና፡፡ ሆኖምእነዚህን ሃሳቦች ለትንታኔ በማጠቀምሂደት ደራሲያንን በቀጥታ ሳይሆን ቀደምሲል ስለ ተረክ ምንነት በተጠቀሰበት ክፍል በቀረበዉ ማሳረት በትረካ ዉስጥእንዴት እንደሚታዩ ለማዳሰስ ይሞከራል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ባለዉ ክፍል ተረካዊ ስነምግባር በተለያዩ የአማርኛ ስነጽሁፍ ታሪካዊ ምዕራፎች ዉስት እንዴት እንደሚታይ ለማዳስ ሜካራ ተደርጓል፡፡ (የታሪክ ክፍፍሉ የተወሰደዉ ጌራርድ (1971) ን ተከትሎ ሲሆን እሱ ካጠናቸዉ ታሪካዊ ግዜያት ወዲህ ያሉት በአትኝዉ የተጨምሩ ናቸዉ)

## 3.የተረካዊ ስነ ምባር ታሪካዊ ቅኝት

በዚህ ክፍል በእያንዳንዱ የአማርኛ ስነ-ጽሁፍ ዘመን ምን እንደሚሞስል ለሞየት እንሞክራለን

### 3.1. ቅድመጦርነት ዘመን

ይህ ጊዜ ሚሞላከተዉ ከጣልያን ወረራ በፊት የነበረዉን የስነጽሁፍ ታሪክ ሲሆን ጠቅለል ባለ ሜልኩ ሲገለጽ ይህ ግዜ ፈርቀዳጅ የስነጽሁፍ ስራዎች የወጡበት እና አማርኛ ከዘሜናዊ የስነጽሁፍ አጻጻፍ ጋር ትዉዉቅ የጀሚረበት ግዜ ነዉ፡ ይህ ዘመን ለኢትዮጵያን ጸሃፍት አስቸጋሪ ዘመን ነበር ማለት ይቻላል፤ ምክንያቱስ ቢሉ በአንድ በኩል ዘሜናዊ የድርሰት አጻጻፍ በራሱ አዲስ በሚሆኑ ደራስን ያንን ለሜልሜድ የሚከፍሉት ማስዋዕትነት ቀላል የሚባል ስለማይሆን እና፤ በሌላ በኩል ደግሞእኒሁ ጸሃፍት የለሜዱትን ጥንታዊ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ አጻጻፍ ዘዴ (ሁሉምማለት ይቻላል በዚህ ዘመን የነበሩ ጸሃፍት የቤተክህነት ትምህርት ዉስጥ

ያለፉ ናቸዉ) ትተዉ ወደ አዉሮጳዊን የአጻጻፍ ስልት ለመግባት ሂደቱ አስቸጋሪ ስለሚሆን የሚሉ ማላምቶችን ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ያም ሆነ ይህ በዚህ ዘመን ብቅ ያሉት የስነጽሁፍ ስራዎች ምንምእንኳ የአዎሮጳዉያን ስነጽሁፎች ተጽእኖ ያረፈባቸዉቢሆንም(በተለይ ከቅርጽ አንጻር) የራሳቸዉን ማንነት ግን ለመፍጠር የቻሉ ናቸዉ፡ በአማርኛ ስነጽሁፍ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚስማሙት የዚህ ዘመን የስነጽሁፍ ስራዎች ማሰረት ጣዮች ብቻ ሳይሆኑ ኢትዮጵያዊዉን የስነጽሁፍ ይትባህል ከዘመናዊዉ ጋር አጣጥመዉ ማቅረብ የቻሉ ዘመን አይሽሬ ስራዎች ናቸዉ፡

ከተረካዊ ስነ-ምግባር አንጻር ስንመለከታቸዉ ቀደም ሲል እንደ ማምግሚያ ነጥብ ያስቀመጥናቸዉን አራት የስነምግባር መርሆዎች አሟልተዉ እናገኛቸዋለን፡፡ የዚህን ዘመን የስነጽሁፍ ስራዎች ተረካዊ ስነምግባር ጠቅልለ ባለ መልኩ ለማቅመጥ የዮናስ አድማሱን (2001፡ 13) አባባል ማጠቀምበቂ ነዉ፡ እንደ ዮናስ አገላለጽ ይህ ዘመን "የልብወለድ ታሪክን ዳራ ፋና ተከትለዉ አዲስ እና ዘመናይት ኢትዮጵያን ለማንባት ብዕራቸዉን አንስተዉ የለዉጥን አስፈላጊነት በተለያየ መንገድ፤ በለዘበና ትህትና ባልራቀዉ ስልት ያቀነቀኑ ደራስያን" ዘመን ሲሆን ደራስያኑም በእሳቸዉ አገላለጽ "ትሁታኑ ፋና አብሪዎች" የሚል ስም ተሰጥቷቸዋል፡፡

በዮናስ ገለጻ ማሰረት የዚህ ዘመን የስነጽሁፍ ስራዎች ማህበራዊ ብቻ ሳሆን አገራዊ ጉዳዮችን ሲያነሱ ማህበረሰባቸዉን ማዕከል ባደረገ መልኩ ሲሆን ለዉጥ ናፋቂነታቸዉንም በትህትና ምክር በሚመስል መልኩ ያቀርባሉ፡፡ የአተራረክ ስልታቸዉም ቢሆን ምን ያክል ምጡቅ ብቻ ሳይሆን ተለምዷዊዉን የአጻጻፍ ስልት የተከተለ እንደነበር ለማሳየት አስፋዉ ዳምጤ (2001፡ 115) ያሉትን እንደ ማሳያ መጥቀስ ይቻላል፡፡ አስፋዉ የዚያን ዘምን አንድ ደራሲ ጠቅሰዉ እንደጻፉት የልብወለድ ታሪክ በአገላለጽ ረገድ ሲታይ "አማርኛዉ ቅልጥፍ ያለ፣ ለአንደበት ተስማሚ፣ ለጆሮ ያልገለማ ላንባቢዉ የሚሞች ለሰሚዉ የማይሰለች እንዲሆን አድርጎ ነዉ የጣፈዉ፡ ምስል ከሳች ድንቅ ገለጻዎች የሞሉበት ለዘማጽሁፍ ነዉ" ብለዋል፡፡ ልብወለድ ታሪክ ብቻ ሳትሆን ሌሎችምበዚህ ዘመን የተጻፉ ስነጽሁፍ ስራዎች በትረካ ስልታቸዉ ተመሳሳይ ባህሪ እንዳላቸዉ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ ባጠቃላይ ቅድመ ጦርነት ዘመን የአማርኛ ስነጽሁፍ ስራዎች ተረካዊ ሰነምግባርን በተምላከተ ምሉዑነት የሚታይባቸዉ ናቸዉ ማለት እንችላለን፡፡

### 3.2. ድህረ-ጦርነት ዘመን

ምንም እንኳየ 1928ቱ የጣልያን ወረራ የኢትጵያን የስነጵሁፍ ታሪክ ሂደት ለተወሰነ ግዜም ቢሆን ቢያደናቅፈዉም ኢዮዊንን ግን ከመፍተር አላቆማቸዉም በጦርነት ዉስም ሆነ ዉድርሰት ደርሱ ነበር፡፡ ጣልያን ተባርሮ ንጉሱ ወደ መንበረ ስልጣናቸዉ ከተማለሱ በኋላ ጸሃፍት የፈጠራ ስራዎቻቸዉን ለህዝብ ለማድረስ አልዘገዩም፡ ቀደም ሲል ከነበረዉ ዘመን ጵሃፍት የቀሰሙትን የስነጵሁፍ ልምድ በልጥ አጎልብተዉ እና አሻሽለዉ ዘመን አይሽሬ ስራዎቻቸዉን ማበርከት የጀመሩች ወዲያዉ ነበር፡፡ ይህ ዘመን የአማርኛ ስነ-ጵሁፍ ልዕልና ዘመን መሆኑን ብዙዎቹ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ ሆኖም ከተረካዊ ስነ-ምግባር አንጻር ስንማለከተዎ ይህ ዘመን እንደቀደመዉ ዘመን ማሉዕ ነዉ ለማለት አያስደፍም፡ የዚህ ትናት ትኩረት ልብወለዶች ላይ በመሆኑ በዚህ ዘመን ከተጸፉት ዉስጥ የተወሰኑትን ለአብነት እየጠቀስን ለማየት እንሞክራለን፡፡ እንደ ዮናስ (2001፡ 16) አገላለጽ በዚህ ዘመን ያሉ ጸሃፍት እንዲህ ነበሩ ብለን የቁርጥ የለየለት ዉህድ ሆነ ማለዩ ለማዉጣት ያስቸግራል፡፡ "ድብልቅልቅ ነዉ፡ ሚስቶ ነዉ፡ አንድ ዉህድ የሆነ እንደሃረግ ተማዞ ሊወጣ የሚቻል ማለዩ ካለ አብዘኞቹ አለባብሶ ሚረስ ሳይሆን ስር ነቀል ለዉጥ ያስፈልጋል ወደሚለዉ አቋም መማጣታቸዉ ነዉ፡" በዚህ ድብልቅልቅ መማንነት ዉስጥ ታዲያ ምን አይነት ተረካዊ ስነ-ምግባር ይስተዋል ነበር፡፡ ስርነቀል ለዉጥ ናፋቂ ልብወለዶች ዉስጥ ያሉ ገጸ ባህያት የግጭት ምክንያቶች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ናቸዉ፡ ብዘዙዎቹ የማህበረሰባዊ ፖለቲካ ስሪቱ እንደ ግጭት ምንጭነዉ፡ የህን ማሻ በሚድረግ እነደ ፍቅር ሰክምቃብር ያሉቱ ገዥን ከጭሰኛ ሲያጋጩእንደ ካድማስ ባሻገር ሉት ደግሞ ዘመናዊነትን ከ ባህላዊለት ያጋጫሉ እነደ አደፍስ ያሉቱ ደግሞ በየደረሱበት የማህበረሰብን እሴቶች በመናድ ላ ተጠመዱ ገጸ ባህርያት በሚፈጥሩት ግጭት ታሪካቸዉን ይነግራሉ፡፡ በሁሉም በኩል የሚስተዋሉት ግችቶች ስነምግባራዊ እሴታቸዉእንዴት ነዉ ብለን ስንጠቅ ምናገነዉ መልስ እንደ ጸሃፊዎቻቸዉ ባህሪ የተለያ ነዉ፡ ለአብነት ካድማስ ባሻገርን ስንወስድ በገጸ ባህሪያቱ ድርጊት የምናየዉነባር ማህበረሰባዊ እሴቶችን በማኮሰስ አዲስ እና ከነባሩ ፍጹምተቃራኒ የሆነ አስተሳሰብን ማድነቅ ነዉ፡ አበራ ጓደኛዉየአበራን ታላቅ ወንድም የሚማግቱበት አግብብ፡ ሉሊት ማንነቷን የምትገልጽበት መንገድ እና አጠቃላይ ገጸባህርቱ የተሳሉበት ሁኔታ ስነምግባራዊእሴትን በተላበሰ መልኩ ነዉ ማለት ያስቸግል፡፡ በቀደመዉ ዘመን የነበሩ የስነጵሁፍ ስራዎች ዉስጥ የሚገኙ ገጸ ባህርያት ከነበራቸዉለዉጥን የሚብኩበት መንገድ ባፈነገጠ መልኩ ትህትና የራቀዉ ተቃዎሞ የሚያሰሙ ገጸባህርት ናቸዉ፡ የአደፍስ ለዉትን ሚብክበት መንገድ የባሰ ነዉ፡ ገጸ ባህሪዉ እሱ የሚያስበዉን እንጅ ለማህበረሰብ የሚቱቅመዉን ነገር ሲያደርግ አይስተዋልም፡ የአደፍርስ ድፍረት እምነትን በእዉቀት ለመቀየር እስከመሞከር ደርሳል፡፡ ይህ አይነቱ የገጸባህሪ አሳሳል ስነምግባራዊ

ነዉወይ ብለን ስንጠቅ አላማዉምንምይሁን ምንምቀደምሲል ካስቀመጥናቸዉየኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍ ተረካዊ ስነምግባር ሚሊለጭዎች አንጻር ተቀባነት የሌላቸዉ ናቸዉ፡ በዚህ ዘመን ከታዩ የስነጽሁፍ ስራዎች ዉስጥ በዚህ ጥናት አቅራቢ አስቴት በተረካዊ ስነ-ምግባር አቻ የማይገኝለት ፍቅር እስከመቃብር ነዉ፡ የፍቅር እስከመቃብር ዋነኛ የ ጥነካሬዉ ምንጭ ያለዉ የተረካዊ ስነምግባር ትንካሬ ይመስለኛል፡፡ ለዉጥ ናፋቂዉ ጉዱ ካሳ ተቃዉሞዉን የሚያሰማበት መንገድ ትህትና ያልተሌዉ ነዉ ማለት ይቻላል፡፡ ፊታዉራሪን የሚያስረዳበት መንገድ ትንሽምቢሆን መዳፈር የሚታይበት ቢሆንምየታናሽ እና የታላቅ ግንኙነት የጣሰ ነዉ ለማለት አስደፍም፡ ከሁሉም በላይ ዘህ ልብወለድ ተረካዊ ስነምግባር ጎልቶ የሚታየዉ በአተራረክ ስልቱ ነዉ፡ የቃላት ሚጣዉየድርጊት ገለጻዉፍጹምኢትዮጵያዊ ስነምግባርን የተላበሰ ነዉማለት ይቻላል፡፡ ለዚህምማሳያ ይሆን ዘንድ አንድ ምሳሌ እንጥቀስ፡፡

የፊታዉራሪ ማሻሻ ባለቤት ሒያጅ (አመነዝራ) መሆናቸዉበሙጽሃፉ ተደጋግሞተገልጾ ይገኛል፡፡ ይህን ተግባራቸዉግን ከማን ጋር እና እንዴት እንደሚፈጽሙበግልጽ አይነገረንምህን ማድረግ ኢትዮጵያዊ ስነምግባር አይደለም እና፡፡ ይለቁንስ ተራኪዉ "ቡን ተጠርተዉ ሄዱ ብሎ" ብቻ ይጠቁመናል፡፡ እንዲህ አይነቱ አነጋገር ስነምግባራዊ ከመሆኑም ባሻገር ትህትናንም ያሳያል፡፤ ተራኪዉልብወለዱ ለሚወከወለዉ ማህበረሰብ ስነ-ምግባራዊ እሴቶች ራሱን ያስገዘ መሆኑን ማየ ት ይቻላል፡፡

ጠቅልል አድርገን ስንማለከቱ የዚህኛዉ ዘመን የስነ-ጽሁፍ ስራዎች ከተረካዊ ስነመግባር አንጻር በተለያየ መደብ ሊቀመጡየ ሚችሉ ናቸዉማለት ይቻላል፡፡

### 3.3. ድህረ-አብዮት ዘመን

በዚህ ዘመን የታዩት የስነጽሁፍ ስራዎች እንደ ቀደመዉዘመን ሁሉ ድብልቅልቅ የሚባል ማንነት ያላቸዉ አይደሉም፡ በተለይም በዘመኑ መጀመሪያ ላይ ብቅ ያሉት ስራዎች አብዮታዊነትን የሚሰብኩ የአብዮቱ ዘብ የሆኑ ነበሩ፡፡ ግዜዉየለዉጥ ነበር እና በስራዎቻቸዉየሚስሏቸዉ ገጸ ባህርያት የለዉጡአቀንቃኝ መሆናቸዉአያስደንቅም፡ ለዉጡምአብዮታዊ ስለነበር በገጸ ባህርያት መካከል የሚ ሳዉ ግጭት በለዉጡ ደጋፊ እና በለዉጡ ተቀዋሚ መካከል ነበር፡፡ ስለሆነ ምየእነ ዚህን የስነጽሁፍ ስራዎች የተረካዊ ስነምግባር እሴት በዚህ ጥናት ላይ እንደ መ ለጫአድርገን ባስቀመጥናቸዉ መርሆዎች መዳኘት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ገጸባህርያት በግብርምበስነምግባርምከ ኢትዮጵያዊነት ይልቅ ለሎች ሶሻሊስት ሀገራት የቀረቡ ናቸዉ፡ ስለመደብ ልዩነት፣ ስለህብረተሰባዊነት፣ እና ስለማሰሉት አብዮታዊ መርሆዎች ሲሰብኩ

ነባሩን ንቀዉ ብቻ ሳይሆን አጣጥለዉም ነበር፡፡ የአዲሱ ቡሆ የነባሩ እርሾ እንደሚያስፈልገዉ ረስተዉ ነበር፡፡ ነባሩን አዉድመዉ የአዲሱን እድገት የሚናፍቁ ይመስላሉ፡፡ ይህ ባህሪያቸዉ በጠቅላላዉ ሲታይ ተረካዊ ስነምግባር ጉድለት የነበረባቸዉ ናቸዉእንድንል ያስገድደናል፡፡

ይህ የይዉደም መርህ በትረካቸዉም ዉስጥ ይስተዋላል፡፡ ባብዛኞቹ በአዲስ ቴክኒክና ፈጠራ (expermentation) ላይ ያተኮሩ ይመስላል፡፡ የበዓሉ ግርማአብዮታዊ ልብወለዶች እና የዳኛቸዉ ወርቁ "አደፍርስ" ለዚህ ማሳያ ናቸዉ፡፡ ነበሩ የተረት አይነት አተራረክ ያተሙቻቸዉ አይመስልም፡ ይህ አይነት ትረካ በራሱ ችግር ነዉባይባልምይሕ ጥናት ይዞት ከተነሳዉርዕስ አኳያ ስናየዉ ያ ቀደምባለዉዘመን ስነምግባራዊ ነዉስንል እንደነበረዉ በሁሉም የእድሜ ክልል ላለ አንባቢ የሚስማማ የአተራረክ ስልት ባለመከተላቸዉ ተረካዊ ስነምግባርን ያሟሉ ናቸዉለማለት አያስደፍርም፡

ከነዚህ አብዮታዊ የድርሰት ስራዎች ለየት ያለ ቅርጽ እና ይዘት ይዘዉብቅ ያሉት የዚህ ዘመን ስራዎችን በተለየ ቡድን ከልሎ ማየት ተገቢ ነዉ፡ የነ ሲሳይ ንጉሱ፣ የነ ፀሃይ መላኩ፣ የነ ፍቅረ ማርቆስ ደስታ እና ሌሎችምስራዎች በዚህ ቡድን ዉስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸዉ፡

እነዚህ ስራዎች ከአብዮታዊነት ወጥተዉአንድንዶቹ ግላዊ ፍላጎት ላይያተኮሩ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ማህርዊ ችግሮችን ተረካቸዉ ማጠንጠኛ አድርገዉ ብቅ ብለዋል፡፡ እነዚህ ልብወለዶች በነሱ ዘመን ከተደረሱት አብዮታዊ ልብወለዶች አንጻር ስንመለከታቸዉየተሻለ ተረካዊ ስነ ምግባር ሚስተዋልባቸዉናቸዉማለት እንችላለን፡ ፡ የገጸባህርያት አሳሳላቸዉ፣ በእነሱምመካከል የሚፈጥሯቸዉግጭቶች ከማህበረሰቡ ልማድና ወግ ጋር የሚስማሙእና ቀደምሲል በዚህ ጥናት መጀመሪያ ላይ ያስቀመጥናቸዉን ኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍ የስነ ምግባር እሴቶች ከሞላ ጎደል የሚያሟሉ ናቸዉ ለማለት እንችላለን፡፡

በአጠቃላይ ተረካዊ ስነምግባር በዚህ ዘመን የስነጽሁፍ ስራዎች ላይ ሲታይ እንደየ ስራዎች ተፈጥሮ የሚለያይ በመሆኑ በአንድ ጠቅልል ባለ አገላለጽ ለማስቀመጥ ያስቸግራል፡፡ በመሆኑምበሁለት ከፍለን አብዮታዊያን ጽሁፎች ከተረካዊ ስነምግበር የራቁ፤ እንዲሁም ማህበረሰባዊያንን ለተረካዊ ስነምግባር የቀረቡ ናቸዉ ብለን ማጠቃልል እንችላለን፡፡

### 3.4. የአሁኑ ዘመን

በዚህ ጥናት የአሁኑ ዘመን ተብሎ የተጠቀሰዉ አሁን በስልጣን ላይ ያለዉ መንግስት ስልጣን ከያዘበት ጀምሮ ያለዉ ግዜ ነዉ፡፡ ይህ ዘመን በብዙ ምክንያቶች ከቀደሙት ዘመናት የተለየ ባህሪ ያለዉ እና እንዲህ ነዉ ብሎ አንድ ጥቅልል ስም ለማስጠት የሚያስቸግር ነዉ፡፡ ይህ አይነተ ብዙነት በስነጽሁፉም ዉስጥ ጎልቶ ይታያል፡፡ ምንም እንኳ የአንድ ዘመን ስረዎች ናቸዉ የሚያስብላቸዉ ባህሪ ባይታጣባቸዉም (ወደኋላ እንማለከተዋለን) ልክ እነ ደቀደሙት ዘመናት ስነጽሁፎች በጥቅል ለመግለጽ ከባለፉትበበለጠ አስቸጋሪ ሆኑ እናገኘቸዋለን፡፡ በዚህ አስጨጋሪ ሁኔታ ዉስጥም ቢሆን በዘሙ ከተጻፉት ዉስጥ ልቀዉ (ጎልተዉ) የወጡት ላይ በተናጥል በማተኮር ተረካዊ ስነ-ምግባር በዚህ ዘመን ምን የማስላል የሚለዉን ለመጫከት እንሞክራለን፡፡ ዮናስ (2001፡ 118) ይህን ዘመን ከስነጽሁፍ አንጻር ሲገልጹት "ንቃትምትጋትም ያጠጠበት" ይሉታል፡፡የእሳቸዉ ትችት በጸሃፍት ትጋት እና ንቃት ላይ ያተኮረ ይማስላል፡፡ በተለይም የቅዉቀት እና የክህሎች ችግር ጎል እንደሚታይ ጠቆም ለማድረግ የፈለጉ ይማስላል፡፡ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የአሁኑ ዘመን ስነጽሁፍ ባብዛኛዉ(ሁሉንምማለት ይከብዳል) ማጠጠያየለበት ነዉበሚለዉይስማማል ሆኖምከ ዮናስ በተለየ ማጠጡየበዛዉበ ስነጽሁፍ ስራዎች የተረካዊ ስነ ምግባር ላይ ነዉየሚል ግምግ ማአለዉ፡፡

ተረካዊ ስነ ምግባር በኢትዮያ ስነጽሁፍ ዉስጥ እየተጓደለ የመጣዉከሁለተኛዉዘመን ጀምሮ እንደሆነ ቀደምሲል አይተናል፡፡ ከዛ ግዜ የጀሚ "ኢ-ስነምግባራዊነት" አሁን ላይ ሲደርስ የባሰበት ይማስላል፡፡ ለዚህ አባባል ማስረጃዎችን እንጥቀስ፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፉን የጻፈዉበ ዘመናችን የአማርኛ ረጅምልብወለዶች ላይ ነዉ፡፡ በሚሆኑምለማስረጃነት የሚጠቀሚዉበደንብ ሚያ ቃቸዉን እና ጥልቅ ንባብ ያደረገባቸዉን ሶስት ርጅም ልብወለዶች ነዉ "የቡርቃ ዝምታ"፣ "ግራጫቃጭሎች" እና "ዴርቶጋዳ"፡፡ ጸሃፊዉበነዚህ ልብወለዶች ወካይነት ስለ ዘሙ ስነጽሁፍ መናገር አግባብ ነዉ ብሎ ያምናል ምክንያቱምእነዚህ ልብወለዶች የዚህን ዘመን መጀሚያ አጋማሽ እና የቅርብ ግዜ በቅደምተከተል ከመወከላቸወዉምበተጨሚ በስፋት ተነበዉበአንባቢያን ዘንድየራሳቸዉቦታ ይዘዉማ ኙበሚሆናቸዉነዉ፡፡

ቀደምባለዉክፍል ስለ ተረካዊ ስነ,ምግባረ በተነ ተነ ዉእና እንደ ማ ሻ ባስቀመጥነ ዉ ማስፈርት ማሳረት እነዚህን ስራዎች ስንገመግማቸዉ ብዙ ጉድለቶች የሚስተዋሉባቸዉ ሆነ ዉ እናገኛቸዋለን፡፡ እነዚህ የስነ ጽሁፍ ስራዎች አንዳንዶቹ( ለምሳሌ የቡርቃ ዝምታ) ማህበራዊ እሴትን መናድ ብቻ ሳይሆን ማህበረሰብን እራነ ለማፍጋት ታስበዉ የተጻፉ ማስላሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ (ለምሳሌ ግጨ ቃጭሎች) እንደቀደሙት የስነ ጽሁፍ ስራዎች ማህበረሰብን ከመተቸት ይልቅ በማህበረሰብ ላይ ለማላገጥ ብቻ የተጻፉ ይማስላሉ፡፡ ሌሎቹም (ዴርቶጋዳ ለማሰሌ) የራሳቸዉን ማህበረሰብ ፈጥረዉ ስለዛ ብቻ ሊነ ግሩን የሚሞክሩ እና የራችንን አለምእረስተን በነ ሱ አለምእንድንደማምየተራፉ ይማስላሉ፡፡ ሁሉም ግን አንድ ነገር ማሳስላቸዉል፡ ግለኝነ ት፡፡ እነ ዱ ካንዱ ጋ የሚጋራዉ የቅርጽም ሆነ የጨብጥ አንድነ ት ካለመኖሩ ባሻገር በዉስጣቸዉ አቅፈዉ የያዟቸዉ ገጸ ባህርያትም ሲሚሚሙ ግለኝነ ትን (individualism) የሚያጠቃቸዉ ሆነ ዉ ይገኛሉ፡፡ (ደመቀ፤ 2006) ይህ ግለኝነ ት ከተረካዊ ስነ ምግባር አንጻጻር ተቀባይነ ት የሚኖረዉ ጉዳይ አይደለም፡ ቀደምሲል ሳምነ ር ባቀማጠዉ የኢትዮጵያዊያን ጸሃፍት ስነ ምግባራዊ ባህሪ ነገለጸዉ ማሳረት ኢትዮጵያዊያን ጸሃፍት የሚጽፉት ስለ ጋራ ማንነ ት እና የጋራ እሴቶች እንጅ ስለግለኝነ ት አይደለም፡ በሚሆኑም የዚህ ዘመን የስነ ጽሁፍ ስራዎች ከዚህ የራቁ ሆነ ዉእናገኛቻለን፡፡

ሌላዉ በዚህ ዘመን ያሉ የስነ ጽሁፍ ስራዎች የታይባቸዉየተረካዊ ስነ ምግባር ጉድለት የትረካ መነገዳቸዉነ ዉ፡ ሁሉምቀደምሲል እንደ ወካይ ያስቀመጥናቸዉልብወለዶች ላይ ላዩን ሲነ በቡጥሩ የትረካ ስልት ተከትለዉየተጻፉ ይማስላሉ፡፡ ሆኖመጠለቅ ብሎ ለሚሜራቸዉ በሁሉም ስራዎች ዉስጥ የሚገኑ ገጸ ባህርያት ማለት ይቻላል የራሰቸዉ የተሟላ ስብዕና የሌላቸዉ እንዴዉም በተራኪወ የተሸፈኑ ናቸዉልንል እንችላለን፡፡ የዚህ ዘመን ተራኪዎች ትዕግስ አልባ ናቸዉ፡ በተረካቸዉ ዉስጥ መናገር የሚፈልጉትን ገጸ ባህርያት እስኪናገሩት አይጠብቁምባልተገባ መነገድ ልተገባ ጊዜ ራሳቸዉን በገጸባሀሪዉ ዉስጥ ዱለዉ የዘባርቃሉ፡፡ የዚህ ዘመን ተራኪዎች ስንፍና የሚያጠቃቸዉ (loose narrators) ናቸዉ፡ ይህ ባህሪቸዉ ቀደምሲል በነ በሩት ዘመናት ካየናቸዉ ተራኪዎች የተለዩ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ከዚህ ዘመን በፊት በነ በሩት ዘመናት ስነ ጽሁፎች ዉስጥ የምናገኛቸዉ ተረኪዎች (ሁሉምለማለት ቢከብድምባብዛኞቹ) የገጸ ባህሪዉን መብት የሚያከብሩ የእነ ሱን አስተሳሰብ በእሱ ላይ ለመጨን የማይደፍ ነ በሩ ብለን ማፍገር እንችላለን፡፡ ለዛ ነ ዉ ቀደምት የስነ ጽሁፍ ስራዎችን ስናስብ ከተራኪዉ (ደራሲዉ) በፊት ገጸባህርያትን የምናታዉሰዉ፡ በዚህ ዘመን

ስራዎች ዉስጥ ግን ይህ አይነት ተረካዊ ስነ ምግባር ስለሌለ የስራዎቹ ማእያ ደራዎች እንጅ ገጸ ባህርያት አይደሉም፡፡ ለዛነዉ ስለ አኖሌ ሳይሆን ስለ ተስፋዬ ገ/አብ የምንጨነቀዉ(የቡርቃ ዝምታ)፣ ስለ ሜዝገቡ ሳንረዳ ስለ አዳምረታ የምናስበዉ(ግጫ ቃጭሎች) እና ስለነ ሜራኸ ረስተን ስለ ይስሞከ ወርቁ የምናብሰለስለዉ) ይህ ከተረካዊ ስነ ምግባር መርህ አንጻር አ-ስነምግባራዊ ነዉ፡፡ በስነተረክ አስተምህሮማሳረት አንድ ተራኪ ስንፍና የተጫነዉከሆነ ተረኩምአ-ተዕማኒ (unreliable) ይሆናል፡፡ ዕንዲህ አይነቱ የስነጽሁፍ ስራ ደግሞተረካዊ ስነምግባር አለዉለማእት ያስቸግራል፡፡

በዚህ ዘመን የስነጽሁፍ ስራዎች አ-ስነምግባራዊነት ላይ ብዙ ማእት ይቻላል ይገባልም፤ ሆኖምለማሳያነት ይህን ያክል ካልን በቂ ነዉ፡፡ እነዳጠቃላይ ግን ይህ ዘመን ተረካዊ ስነ-ምግባር እጅግ ደክሞየሚስተዋልባቸዉየኢትዮጵያ የስነ ጽሁፍ ዘመን ነዉማእት ይቻላል፡፡

**4.ማጠቃለያ**

በዚህ አጭር ጥናታዊ ጽሁፍ ለማሳየት የተሞከረዉ ተረካዊ ስነምግባር በኢትዮጵያ የስነጽሁፍ ታሪክ ከሄተ ወደ ሄት እነ ሄደ ነዉ፡፡ በቀደሚዉሀተታ እንደተማእከተዉም ወደ ቀረበዉ የስነጽሁፋችን ታሪክ በማጣንቁጥር ተረካዊ ስነ ምግባርም እየደከመ ይመጣል፡፡ ለዚህ ምክንቶቹ ብዙ ናቸዉማእት ይቻላል፤ ሆኖምየዚህ ጥናት አዉድ ይህን ርእስ ስለማየተቃልል ሌሎች ተሜራሜሪዎች ይህን ጉዳይ በጥልቀት ሊዳሱት እና ሜሁራዊ ትንታኔ ሊሰጡምት ገባል የሚል ምክረ ሀሳብአቀርባለሁ፡፡

## ማጣቀሻ ጽሁፎች


Demeke Tassew. 2014. N Arrative Strategies in Selected Amharic novels (from 2000-2010). dissertation: UNISA

Ge'rard, S. A. 1971. *Four African literatures*. California: UCP

Newton Z.A. 1995.Narrative Ethics. HArvard: HUP.

Rudrum, D. 2005. From narrative representation to narrative use: towards the limits of definition. *NARRATIVE*, 13(2): 165-204.

Sumner, C. 1985. Ethiopian literature and philosophy, in *AKSUM THYATEIRA*, edited by Dion, GD. London: THYATEIRA HOUSE: 427-458.

Philan,J..2013. narrative Ethics, in The Living Handbook of Narratology edited by Herman, D. Cambridge: Cambridge University Press: 22-35.

Taddesse A & Ali JA. 1995. *Silence is not golden: a critical anthology of Ethiopian literature.* Lawrenceville: Red See Press.

ዮናስ አድማሱ፡ ፡ 2001፡ ፡ የአማርኛ ስነጽሁፍ ጉዞ፣ በ"መድበለ ጉባኤ"፣ አርታኢ ደረጀ ገብሬ፣ የኢትዮጵያ ደራያን ማህበር፡ ፡

አስፋዉዳምጤ፡ ፡ 2001፡ ፡ የአማርኛ ልብወለድ ጉዞ በ"መድበለ ጉባኤ"፣ አርታኢ ደረጀ ገብሬ፣ የኢትዮጵያ ደራያን ማህበር፡ ፡